# ሥራ የሚበዛባቸው ኢትዮጵያዊያን መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሚችሉበት መንገድ

## <u>ትምህርት-1</u>

<u>መግቢያ</u>፡- የቡድን መሪው የሚከተለውን ይጠይቃል፡- በግልህ መጽሐፍ ቅዱስን መቼ መቼ ታነባለህ? መጽሐፍ ቅዱስን መቼ መቼ ታጠናለህ? ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ላለማንበባቸው የሚሰጡት ምክንያት ምንድነው? በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርጉ፡፡

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ላለማንበብ የሚሰጡአቸው የተለመዱ ምክንያቶች ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንተን የሚመለከትህ የትኛው ነው?

1. እኔ የቤ/ክ መጋቢ ስላልሆንኩ መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ይከብዳል፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስን ሳነብ ይሰለቸኛል፡፡
3. ብዙ ሥራ ስላለብኝ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጊዜ የለኝም፡፡
4. መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚጠና አላውቅም፡፡
5. መጽሐፍ ቅዱስ ከሕይወቴ ጋር አይዛመድም ብሎ ማሰብ፡፡

**<u>የሚከተለውን አንብቡና ውይይት አድርጉበት</u>**

ጄ.አይ.ፓኬር (J.I.Packer) የተባለ ፀሐፊ የሚከተለውን ብሏል፡- ‹‹ እኔ ሰይጣን ቢሆን ኖሮ ከቀዳሚ ዓላማዎቼ አንዱ የሚሆነው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት እንዳይመረምሩ ማድረግ ነው››፡፡

ሌላው ሐዋርድ ሄንድሪክስ (Howard Hendricks) የተባለ ፀሐፍ ደግሞ የሚከተለውን ብሏል፡-‹‹ይህ መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ ማለቱ ነው፡፡) አንተ ወደ ሐጢአት እንዳትጠጋ ያደርጋል፡፡ ወይም ሐጢአት አንተ ወደዚህ መጽሐፍ እንዳትጠጋ ያደርጋል፡፡››

**የሚከተለውን አንብብ፡፡**

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ሰይጣን ያውቃል፡፡ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያውቁ፣ እርሱን እንዲወዱትና እንዲያገለግሉት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር ሰይጣን ያውቃል፡፡ ስለዚህ ሰይጣን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰሙ ለማድረግ ይጥራል፡፡

ብዙ ኢትዮጵያዊያን ስብከትን ለመስማት ረጅም መንገድ ይጓዛሉ፡፡ ግን ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን በግላቸው ከፍተው አያጠኑም፡፡ ይህንን ከማድረግ ይልቅ ስለ ሥራና ስለ ስፖርት ማውራት ይቀላቸዋል፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ እውነቶችን በግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን ከፍተው ለሚፈልጉ ሰዎች እግዚአብሔር ታላቅ ሽልማት ሊሰጥ ተስፋ ቃል ገብቶላቸዋል፡፡

መዝ፡19፡7-11 አንብብ፡፡ ከዚህ ክፍል የምትማረው ምንድነው?

በሉቃ፡10፡38-41 ላይ ስለ ማርታና ማሪያም <u>**ታሪክ በቃል ተናገር፡፡**</u>

ማርታ የምትሠራው ሥራ ስህተት ነው ማለት አይደለም። እሷ እንግዳን በመቀበል ሥራ ተወጥራ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ምን አላት? ከዚህ ታሪክ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብና መንፈሳዊ ብስለት ለማግኘት የግድ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ መግባት አያስፈልግህም። ልክ እንደ ማሪያም መሆን ትችላለህ። ነገር ግን ሥራ የበዛባቸው ሴቶችና ወንዶች እንደ ማሪያም እግዚአብሔርን ለመስማትና ቃሉን ለማንበብ ማድረግ ያለባቸው ጊዜ ማመቻቸት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በጣም አስፈላጊ ናቸው ከምትላቸው ነገሮች ሁሉ ቀዳሚ ማድረግ አለብህ።

1ጴጥ፡2፡2 አንብብ። ‹‹ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።›› የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ግቡ ምንድነው? ስለ አመለካከት ከዚህ ክፍል የምትማረው ምንድነው?

**ምን ማድረግ እንችላለን?** እቅድህን በሚከተለው ባዶ ቦታ ሙላ።

1. መጽሐፍ ቅዱስን መቼ ማጥናት እንደምትችል ወስን። ለማጥናት የሚመችህ ጊዜ የትኛው ነው? ---------------------------------------------
2. የምታጠናበት ቦታ የት ነው? --------------------------------
3. ለስንት ሰዓት ታጠናለህ? -------------------------------------
4. ከእግዚአብሔር ጋር ሆነህ እቅድህን ፈጽም።

ከዚህ በታች ያሉ ሀሳቦች በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ እንድንወስድ ያበረታቱናል። እነዚህን ሀሳቦች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በሕብረት አንብቡ።

1. መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው በመንሳዊ ሕይወቱ ያድጋል፤ይለወጣል።
2. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው የእግዚአብሔርን ድምጽ ይሰማል። መንፈስ ቅዱስ ሊያስተምረው የፈለገውን ሁሉ ያስተምረዋል።
3. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው የእግዚአብሔርን ማንነትና እርሱ በምድር ላይ የሚሠራውን ሥራ መረዳት ይጀምራል።
4. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው ለአስቸጋሪ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ያገኛል። ሰዎች መስማት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል በንቃት ሲያነቡ ቃሉን ማስታወስና የበለጠውን መማር ይችላሉ።
5. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው የራሱን ማንነትና መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እንደሚያጠና ያውቃል።
6. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠብቃል።
7. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው መጽናናትን፣ምሪትን፣ብርታትንና ከሐጢአተኝነት ስሜት ነፃ መውጣን ይለማመዳል።
8. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው ሌሎችን መርዳት የሚችልበት አቅም ይኖረዋል።
9. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ መከራን በድፍረት ይጋፈጣል።
10. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው ውሳኔዎችን በጥበብ ይወስናል።

11. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ የሚያነብ ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ ያውቃል፡፡

ሰይጣን ከእግዚአብሔር ቃል እንዳያወጣን በፍጹም ልብ መወሰን አለብን፡፡ ራስህንና ጊዜህን ለእግዚአብር ቃል እንድትሰጥ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ፀልይ፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛ የሆነ የቃሉን ጥማትና ረሃብ እንዲለቅብን እንፀልይ፡፡ <u>አሁን በቡድን ፀልዩ</u>፡፡

**የቤት ሥራ**

አንድ ወረቀት ውሰድና ከዚህ ትምህርት ለማሰላሰል የምትፈልገውን አንድ ሀሳብ ፃፍ፡፡ ይህን የፃፍከውን ክፍል በየቀኑ ማየት በምትችልበት ቦታ አስቀምጥ፡፡ ወደ ቀጣዩ ትምህርት ስትመጣ ከባለፈው ትምህርት የተነሣ በሕይወትህ የሆነውን ነገር ለቡድንህ አባላት ለማካፈል ተዘጋጅ፡፡

ወደ ቀጣዩ ትምህርት ከመሄድህ በፊት የሚከተለውን ሀሳብ አንብብና ከጓደኛህ ጋር ተወያይ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያደርጋቸው አሥር ነገሮች፡፡ በጆን ፓይፔር (John Piper) የተፃፈ፡፡

1. **መጽሐፍ ቅዱስ የመታዘዝ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እምነትን በውስጣችን ይፈጥራል፡፡**
   ‹‹እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡›› (ሮሜ፡10፡17)
2. **መጽሐፍ ቅዱስ ከሐጢአት ሁሉ ነፃ ያወጣል፡፡**
   ‹‹እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል፡፡›› (ዮሐ፡8፡32)
3. **መጽሐፍ ቅዱስ ከሰይጣን እሥራት ነፃ ያወጣል፡፡**
   ‹‹የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም፡፡ ደግሞም ምናልባት እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንስሐን ይሰጣቸዋልና ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥመድ ወጥተው ወደ አእምሮ ይመለሳሉ ብሎ የሚቃወሙትን በየዋህነት ይቅጣ፡፡›› (2ጢሞ፡2፡24-26)
4. **መጽሐፍ ቅዱስ ይቀድሳል፡፡**
   ‹‹በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው›› (ዮሐ፡17፡17)
5. **መጽሐፍ ቅዱስ የተበላሸውን ስነምግባር አስወግዶ እግዚአብሔርን በሚፈልግ ልብ ይሞላል፡፡**
   (2ጴጥ፡1፡3-4)
6. **መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅርን ይጨምራል፡፡**
   ‹‹----የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እፀልያለሁ፡፡›› (ፍልጵ1፡10)
   ‹‹የትዕዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፡፡›› (1ጢሞ፡1፡5)
7. **መጽሐፍ ቅዱስ ያድናል፡፡**

‹‹ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና፡፡›› (1ጢሞ፡4፡16)

‹‹ይድኑ ዘንድ የእውነት ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ----፡፡›› (2ተሰ፡2፡9)

8. **መጽሐፍ ቅዱስ ደስታን ይሰጣል፡፡**

‹‹ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ፡፡›› (ዮሐ፡(15፡11)

9. **መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ማንነት ይገልጣል፡፡**
‹‹እግዚአብሔርም ደግሞ በሴሎ ተገለጠ፤ እግዚአብሔርም በእግዚአብሔር ቃል ለሳሙኤል በሴሎ ይገለጥ ነበር፡፡ የሳሙኤልም ቃል ለእሥራኤል ሁሉ ደረሰ፡፡›› (1ሳሙ፡3፡21)

10. **ስለዚህ** ለቤቴ ደስታ፣ለሕይወቴና ለአገልግሎቴ መሠረቱና ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር የዘላለም ተስፋ የሆነኝ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡